50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
Telephone: 1300 650 172
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

Amharic | አማርኛ

27 ማርች 2025

**ጠቃሚ ወቅታዊ መረጃ ስለ የሰሜን ሜልቦርን (North Melbourne) መኖሪያ ቤት ቢሮ መዘዋወር**

የዳግም ግንባታውን እያንዳንዱ ደረጃ በወቅታዊነት ለእርስዎ ማድረስ እንፈልጋለን። ይህ ደብዳቤ ስለሚከተሉት መረጃ አካተዋል፡-

- የሰሜን ሜልቦርን መኖሪያ ቤት ቢሮን ለማዛወር በመዘጋጀት ላይ
- ዕቅዶች ሂደት ላይ በሆኑበት ወቅት እርስዎን ስለማሳወቅ

**በእርስዎ ቋንቋ የተተረጎመውን መረጃ ለማግኘት ይቃኙ**

**የሰሜን ሜልቦርን መኖሪያ ቤት ቢሮ በመስከረም 2025 ወደ ኣስኮት ቫሌ (Ascot Vale) ይዘዋወራል**

እንደ የ33 ኣልፍረድ መንገድ (Alfred Street) ማሻሻያ ግንባታ የሰሜን ሜልቦርን የመኖሪያ ቤቶች ቡድን በመስከረም 2025 መጨረሻ በ12 ቸርችል ጎዳና (Churchill Avenue), አስኮት ቫሌ (Ascot Vale) ወደሚገኘው አስኮት ቫሌ መኖሪያ ቤት ይዘዋወራል።

የሰሜን ሜልቦርን ቡድን ተከራዮችን መንከባከብ እና መደገፉን ይቀጥላል፣ እና እንደ የዝውውሩ አካል ሆኖ በሰሜን ሜልቦርን ቡድን ላይ ምንም አይነት ለውጥ አይኖርም።

የሰሜን ሜልቦርን ቡድን ተከራዮች የሚያደንቁትን ታላቅ ስራ እንደሚሰራ እና በዚም እንደሚቀጥል እናውቃለን።

የፊት ለፊት ቀጠሮዎችን እና የቤት ጉብኝቶችን በስልክ እና በኢሜል ጨምሮ አሁን እርስዎ በሚያደርጉት ተመሳሳይ መንገድ እርዳታ እና ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።

ለሚደውሉለት ቡድን አሁንም መደወል ይችላሉ።

**አስኮት ቫሌን ለምን መረጥን?**

ብዙ አማራጮችን መርምረን አስኮት ቫሌን በሚከተሉት ምክንያቶች ተመርጧል፧

**ቅርብ ቦታ፡-** የአስኮት ቫሌ መኖሪያ ቤት ቢሮ ከሰሜን ሜልቦርን ሶስት ኪሎ ሜትር ብቻ ነው የሚርቀው። ቢሮው የፍለሚንግቶን (Flemington) መኖሪያ ቤት ቡድን የሚሰራበት ቢሮም ነው።


**የተደላደለ ሽግግር፡-** የአስኮት ቫሌ መኖሪያ ቤት ቢሮ እንደ መኖሪያ ቤት ቢሮ ተቋቁሟል፣ ይህ ማለት ስንዘዋወር ለተከራዮች የምንገኝ መሆናችንን እንቀጥላለን – ይህም ለሁለቱም ለተከራዮች እና ለሰራተኞች ጥሩ ነው።

**አቅም፡-** የአስኮት ቫሌ መኖሪያ ቤት ቢሮ የሰሜን ሜልቦርን ቡድንን ለማስተናገድ በቂ ቦታ አለው።

**ደህንነት እና ተድማምፃነት፡-** ቢሮው ለህብረተሰቡ እና ለሰራተኞቻችን ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን። የአስኮት ቫሌ መኖሪያ ቤት ጽሕፈት ቤት የደህንነት የጥበቃ መስፈርቶችን ያሟላ ሲሆን እንደ የግል መሰብሰቢያ ክፍሎች፣ ቴክኖሎጂዎች፣ መታጠቢያ ቤቶች እና የሰራተኞች ኩሽና የመሳሰሉ መገልገያዎችን አቋቁሟል።

## የአስኮት ቫሌ መኖሪያ ቤት ቢሮ የት ነው የሚገኘው?

12 Churchill Avenue, Ascot Vale




## ዕቅዶች ሂደት ላይ በሆኑበት ወቅት እርስዎን ስለማሳወቅ

በሴፕቴምበር 2025 መጨረሻ የሰሜን ሜልቦርን ቡድንን ወደ አስኮት ባሌ መኖሪያ ቤት ጽሕፈት ቤት ለማዛወር በዝግጅት ላይ ነን። ዕቅዱ እየገፋ ሲሄድ እናሳውቆታለን እናም የሚፈልጉትን እንክብካቤ እና ድጋፍ ማግኘት እንደሚችሉ እናረጋግጣለን።

በሰሜን ሜልቦርን አካባቢ ስለሚሆነው ነገር የበለጠ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ፡-
https://www.homes.vic.gov.au/precincts/north-melbourne-precinct